# *Ethiopian Partnership in the United Kingdom (EPUK)*
*የኢትዮጵያዉያን ትብብር በታላቁዋ ብሪታኒያ (ኢትታብ)*

ኢሜል: ethiopianpartnersuk@hotmail.com
ድረ-ገጽ: www.partners.com

ሚያዝያ 29 ቀን 20006 ዓ.ም

በአስቸኩዋይ የወጣ

## ኢትዮጵያ ዉስጥ በበርካታ አካባቢወች የተፈጸወዉን የሰብአዊ ሙብት ረገጣ በመቃወም የኢትዮጵያዉያን ትብብር በብርታኒያ (ኢትታብ) ያስተላለፈው መግለጫ

ሰሞኑን ኢትዮጵያ ዉስጥ የሰብአዊ ሙብት ረገጣዉ በተለያዮ አካባቢዎች በሚያሳዝን ሁኔታ መቀጠሉ እየተዘገበ ነው። ወያኔ እነዚህን የሰብአዊ ሙብት ረገጣዎች በከፋ መልኩ ያካሄደዉ በአምቦ ከተማና በጎንደር የተለያዩ ኣካባቢዎች ሲሆን በተለይም ራሱ ክልል ብሎ በሰየመው ኦሮሚያ ዉስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰላማዊ ዜጎች ሰልፍ በመዉጣታቸው ብቻ ተጨፍጭፈዋል:: አልፎ አልፎ ወንጀሉን ሲደብቁለት የቆዩ የዉጭ መረጃ ማሰራጫወች ሳይቀሩ ግድያዉን መስክረዋል። ግድያዉ ድብደባዉና ማዋከቡ በከፍተኛ ደረጃ በአምቦ ከተማና በሌሎች አካባቢዎች በማካሄድ ላይ መሆኑ ሲታወቅ የተለያዩ የሀገር ዉስጥና የዉጭ ሃገር የዜና ማሰራጫዎች በስፋት ዘግበዉታል። የእንግሊዝ የመረጃ ማሰራጫ ድርጅት (ቢቢሲ) ከቦታዉ አገኘሁት ባለው መረጃ መሰረት 47 ሰዎች መገደላቸዉን ሲዘግብ አንዳንድ የመረጃ ምንጮች ደግሞ የተገደሉት ሰዎች ቁጥር ከዚያ በላይ እንደሚሆንና ወያኔ እንደተለመደው ለማጣጣል ሲል ቁጥሩን ዝቅ እንዳደረገው ይገምታሉ።

ወያኔ ህዝብ ሳያማክርና ዜጎች ሳይሳተፉበት ከፋፍሎ ለመግዛት እንዲያመቸው ኢትዮጵያን በራሱ ፍላጎት በመሸንሸን ከአማራው ከአፋርና ከሌሎች አካባቢዎች ሰፊ ለም መሬት በመውሰድ ወደ ትግራይ ከመከለሉም በላይ በሌሎቹም የሃገሪቱ ክፍሎች ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉ ካርታዎወችን አዘጋጅቶ ህዝባችንን እርስ በርሱ እንዲጋጭ በቋንቋና በዘር ላይ የተመሠረተ የክልል ወጥመድ ዘርግቶ አገሪቱን እስካሁን ከታየውም በላይ ለከፋ ትርምስ እያዘጋጃት ይገኛል::

ይህ ጠባብ ዘረኛና ሽብርተኛ ቡድን ከሃያ ሶስት አመታት በላይ ሲቆይ ለሰብአዊ ሙብትና ለሰው ሊጆች ነጻነት ግድ የለሽ መሆኑን በተደጋጋሚ አስመስክሮአል:: አሁን በቅርቡም በወገኖቻችን ላይ የፈጸመው ርህራሄ የጎደለዉ የጭካኔ እርምጃ የሃገሪቱን አንድነት ጥቅምና ደህንነት የሚጻረር ተግባር ስለሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ከአለም አቀፍ ሀብረተሰቡ ጋር በመተባበር በአስቸኩዋይ በገለልተኛ አካል እንዲጣራ የሚቻለውን ሁሉ እንዲያደርግና ለተፈፀሙትም ወንጀሎች ተጠያቂ የሆኑት ለፍርድ መቅረብ ይኖርባቸዋል::

በመሃል ሃገር በደቡብና በምስራርቅ ዉስጥም ህዝባችን ለዘመናት ተቻችሎና ተፋቅሮ በሰላም ይኖርበት ከነበረበት ቀየው ግጭት በማስነሳትና በማፈናቀል ወንድማማች ኢትዮጵያዉያንን ለ23 ኣመታት ሲያምስና ሲጨፈጭፍ ቆይቷል። ይሁን እንጂ አንዳንድ የህብረተሰቡ ክፍሎች ይህንን ተንኮሉን በሚገባ ባለመገንዘባቸው የስርዓአቱ የጥላቻና የመከፋፈል ሤራ ሰለባ ለመሆን በቅተዋል። የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን በማስፋት እንቀይራለን በማለት በሚቆጣጠረው የህዝብ ሚዲያ ይፋ በማድረግና በዉስጥ በመቀስቀስ የህዝቡን ስሜት ካስቆጣና ብሶቱንም ለመግለፅ በሰልፍ እንዲወጣ ካነሳሳው በኋላ ለሰልፉ የወጡትን ንፁሐን ወጣቶች ከዚህ በፊት እንዳደረገው ሁሉ በግፍ መግደሉ በድጋሚ አሸባሪነቱንና በህገወጥ መንገድ በሃይል በህዝቡ ላይ መጫኑን የሚያረጋግጥ ነው።

የኢትዮጵያዉያን ትብብር በታላቁዋ ብሪታኒያ (ኢትታብ) ይህንን በአምቦና በሌሎች አካባቢዎች የተፈጸመዉን ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ረገጣ እዬኮነነ የሃገሪቱዋ ባለቤት የሆኑት ሁሉም ኢትዮጵያዉያን ዜጎች ስለሆኑ ወያኔ በሸረበው በቋንቋና በዘር ማንነት የተመሠረተ ከፋፋይ የክልል ወጥመድ ዉስጥ እንዳይገቡ መልእክቱን ያስተላልፋል። ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያዉያን በወያኔ በየጊዜው በሚዘጋጅላቸው የማጭበርበርና የመከፋፈል ሤራ የትግል ሃይላቸዉን አዳክመዉ ጠላት ወደሚፈልገው የጥፋት አቅጣጫ እንዳይሄዱና ለስርዓቱ ጥቃት እንዳይጋለጡ አጥብቆ ያሳሳስባል።

ስርዓቱ ለራሱ እንዲያመቸው በፈጠረው ክልል ላይ እየተረማመደ ማሸበሩን ስለማያቆም ኢትዮጵያዉያን በአሁኑ ሰአት ከላይ በተጠቀሱት አካባቢ ወገኖቻቸው ላይ የሚደረገዉን የሰብአዊ መብት ረገጣ ቸል ሳይሉ በጋራ ሆነው በጥብቅ ማውገዝ ይኖርባቸዋል። ስለዚህ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሃይሉን አስተባብሮ ለአንዴየና ለመጨረሻ ጊዜ ወያኔን ከጀርባው ላይ አሽቀንጥሮ በመጣል ኢትዮጵያን ከጸረ ህዝቡና ዘረኛው ስርአት እጅ ፈልቅቆ ነጻ ለማዉጣት ታጥቆ መነሳት አለበት።

መሳሪያ የታጠቃችሁ ዜጎች በሙሉ ከተጠያቂነትና ከታሪክ ተወቃሽነት ለመዳን ከወገኖቻችሑ ጎን በመቆም አፈሙዙን ወደ ስርዓአቱ በማዞር ወንጀል መፈጸማችሑን እንድታቆሙ ትብብሩ ጥሪዉን አቅርቦላችኋል። በዉጭ አገር የምንገኝ የፖለቲካ የሲቪክ ድርጅቶችና ግንባሮች ከመቸዉም ጊዜ የበለጠ በመቀራረብ የተቀናጀ ስራ በመስራትና የሃገር ዉስጥ ትግሉን በመደገፍ ህዝባችንን ከዚህ አሰቃቂ ስቃይና መከራ ዉስጥ ለማዉጣት አስፈላጊዉን ሁሉ ማድረግ ይኖርብናል።

ድል ሰላምና አንድነት ለነፃነት ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብ

የኢትዮጵያዉያን ትብብር በታላቁዋ ብሪታኒያ (ኢትታብ)

ለንደን (ብሪታኒያ)

ethiopianpartnersuk@hotmail.com